# የዘመናት ጌታ

የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ
ከዚህ ካደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ
አቀርብልሃለሁ የክብር ሰላምታ (2)

**ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩ አባታች**
**ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ላደረሰን ሁላች**

የሰው ልጆች ዕድሜ ጥንቱንም ሲጀመር
ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር
አንድ ቀን አይሞላም እንዳንተ አቆጣጠር(

ስለዚህ አምላክ ሆይ ክቡር ነው ቅዱስ ነው
ወዳንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው
ደካማ ነውና ሰው እድሜ ከራበው (2)

እጅግ አደንቃለሁ የአምላክን ጥበብ
ምድርን በአበባ ሰማዩን በኮከብ
እንዳሸበረቃት አስተውዬ ሳስብ (2)

በከንቱ ጊዜያችን ፈጽሞ እንዳይጠፋ
በርትተን ከሠራን ያላንዳች ነቀፋ
አምላክ የሚሰጠን አለን ሙሉ ተስፋ (2)

ከቶ ካሳለፍኩት ጊዜዬን በዋዛ
ምን ያደርግልኛል ዘመኔ ቢበዛ
ደግሞም በጠቅላላው ዓለምን ብገዛ (2)

ወርኃ ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ
ምድር በልምላሜ ስታጌጥ በአበባ
እናምናለን ላንተ ምስጋና እንዲገባ (2)

# መስከረም ጠባ

መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ
መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ
መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ ኢዮ
መስከረም ጠባ ለኛ ኢዮሃ አበባ
ለኛ እንዲሆነን እድገትና ልማት
ኢዮ ኢዮ አበባዬ ኢዮ
መስከረም ጠባ ለኛ ኢዮሃ አበባ
በተዋህዶ የከበረች እናታችንን
እናከብራለን የጥበብ ሕፃናቶቿ
ሃይማኖት ከምግባር መግባ
ስላሳደገችን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
እናታችን
ጥንትም መሪና አስተማሪ በመሆንዋ
ስላቆየችን ለኛ አጥብቃ
እየተወሳ ባለም ዜና ያኮራናል መስቀላችን
ኢዮሃ አበባ ኢዮ መስከስም ጠባ ለኛ
ኢዮሃ አበባዬ (3)

# የአዋጅ ነጋሪ ቃል

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሃ አየለ
የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካሉ እያለ
ምስርነቱን ዮሐንስ ካስረዳን
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም

ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማው ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንመሥርት ሁላችን
ማለፊያ እንዲሆነን ለመጪው ሀብታችን

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም

ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርኅራኄ በእኛ ላይ ይስፋፋ

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም

ሥጋና ደምህን በብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆነን አምላ ተማጽነናል
ከበደላችንም አንጻን አደራህን
በፋ እንዳንጠፋ እኛ ልጆችህ

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም

# ሆ ብለን መጣን

ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን    መድኃኔዓለም ብለን
ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን    ምዕመናንን ብለን
ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን    ክርስቲያኖች ብለን    (3X)

አበባ አየሁ ወይ ለምለም (2X)

| | | | |
|---|---|---|---|
| ክርስቲያን ወገን | አሜን | ያለህ በምድር | አሜን |
| ለቸሩ ጌታ | »» | ተነሳ እንዘምር | »» |
| ክረምቱ አልፎ | »» | መስከረም ጠባ | »» |
| ሰማዩ ጠርቶ | »» | ኮከቡ በራ | »» |
| ተራራው ሜዳው | »» | እህሉ አፈራ | »» |
| ለዚህ ለአበቃን | »» | ለአደረሰን | »» |
| ለቸሩ ጌታ | »» | ምስጋና ይሁን | »» |

ተነሱ እልል እንበል ለመድኃኔዓለም
ተነሱ እልል እንበል ለአማኑኤል    (2X)

| | | | |
|---|---|---|---|
| እመቤታችን | ቅድስት | እርጂን እባክሽ | ቅድስት |
| በእኛ ላይ ይሁን | »» | የምሕረት ዓይንሽ | »» |
| በአዲሱ ዓመት | »» | ቃል እንገባለን | »» |
| ከክፋት ርቀን | »» | በጎ እንሰራለን | »» |
| ጌታን አምልከን | »» | እንድንኖር | »» |
| እንድንዋደድ | »» | በፍፁም ፍቅር | »» |

አደራ ድንግል ማርያም አትለይን
ፀሐይ ቅድስት ማርያም የአምላክ እናት    (2X)

እቴ አበባሽ እቴ አበባዬ አዬ እቴ አበባዬ (2X)

| | | |
|---|---|---|
| ለአምላካችን ለቸሩ ጌታ | ሃሌ | ሃሌሉያ |
| ክብር ይሁን ጠዋትና ማታ | »» | »» |
| ለአደረሰን ለዚህች ዕለት | »» | »» |
| የዓለም ቤዛ የዓለም ሕይወት | »» | »» |
| አለኝታችን መመኪያችን | »» | »» |
| ለአንተ ብቻ ክብር ይሁን | »» | »» |

አበባ አየሁ ወይ ለምለም (2X)

| | | | |
|---|---|---|---|
| አምላካችን ሆይ | አሜን | በሰማይ ያለህ | አሜን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለዚህ ውለታህ | » » | እናመስግንህ | » » |
| በቸር ጠብቀህ | » » | ስላደረስከን | » » |
| ለመጪው ደግሞ | » » | አደራህን | » » |

መስቀል ብርሃን ለዓለም ዘለዓለም (2X)

ከብረው ይቆዩን ከብረው
በተዋኅዶ ጸንተው
ለሥጋ ወደሙ በቅተው
በጌታ አብበው አምረው
ከብረው ይቆዩን ከብረው
(2X)

# አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በአይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ
} **አዝማች** (2X)

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋ

**አዝማች**...

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ስዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

**አዝማች**...

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣዖት እንድሰግድ ነገሥታት ቢቆጡም
ሁሉም ቢተውኝም ቢጠላኝም ዓለም
ጽናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኔዓለም

**አዝማች**...

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋ

**አዝማች**... (2X)

# አሳልፎ ትናንትናን

አሳልፎ ትናንትናን
አድርሶናል ለምስጋና
ካደረገን የዛሬ ሰው
ክብር ምስጋና ለእርሱ ይድረሰው } **አዝማች…**

ከማኅፀን አውጥተህ ያመጣኸን አንተ ነህ
ሰው አርገህ ፈጠርኸን በእጆችህ ቀርጸህ
መናን የመገብከን በረሃቡ ዘመን
ታላቅ ነህ ብለናል አይተን ሥራህን (2X)

**አዝማች…**

የመከራውን ዘመን የጭንቀትን ወራት
አሳልፈኸዋል በድንቅ ተዓምራት
ሆነሃል አምላካችን መጽናኛ ማረፊያ
ለሚገዳደሩን ሁሉ ማሸነፊያ (2X)

**አዝማች…**

ተራሮች ይፈልሳሉ የራቀውም ይቀርባል
እግዚአብሔር ከረዳን ማን ይቃወመናል
የፀሐዩም ጉዞ በሰማይ ይቆማል
እኛ እስክናሸንፍ ፍጥረት ይታዘዛል (2X)

**አዝማች…**

ባሳለፍነው ጊዜ ብዙ ተምረናል
በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ዓይናችን ተገልጧል
በኃይለኛው ጌታ በአምላካችን ፊት
አራግፈን ጥለናል ያን ሁሉ ጭንቀት (2X)

**አዝማች…**

ወገኖች የነበሩ በፍርሃት ቢሸሹን
በሕዝብ አደባባይ በሐሰት ቢፈርዱብን
በለቅሷችን ጊዜ እንባችንን ያበሰከው
የመጽናናት አምላክ እንዳንተ ያለ ማነው (2X)

**አዝማች…**

## ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብየ መች እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና

ጨለማ ውጦኝ በጠላት አገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
ያለሙን መድህን ወለድሽልን
ከአባቶቼ ርስት ካገር ወጥቸ
በአህዛብ አገር ስኖር ተሸጬ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን ያስረሳሽኝ

ድንኳኑ ሞልቶ ሰው ታድሞ
አስተናበሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርበለሁ ብየ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት ሀሳብ ደመኖ ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን አይቀርም
በማምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም

እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይች አለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባህሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝም
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝም
አላቋርጥም ያንችን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና

ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝም
አንቺን መውደዴን አያስተውኝም
በአህዛብ መሀል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኝኝ እናቴ አደራ

# አቤቱ ፈጣሪያችን

**አቤቱ ፈጣሪያችን መድኃኒታችን አምላካችን (2)**
**ባንተ ላይ ነው ዘላለም ተስፋችን**

ቀንና ሌሊቱን የምታፈራርቅ
አምላክ አንተ ብቻ ሥራህ የሚያስደንቅ

መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ
በረቂቅ ሥልጣንህ ሁሉን የምትገዛ

በበደልነው በደል በሠራነው ሥራ
በትህትና ፈጸምክ ያን ሁሉ መከራ

ሰይጣን በተንኮሉ እንዳያጠምደን
በሕይወት ጎዳና ወዳንተ ምራን

የዘለዓለም አምላክ የፍቅር የሰላም
አቤቱ ተመስገን እስከ ዘለአለም

ያንተ ምህረትና ያንተ ቸርነት
ተነግሮ አያልቅም በሰው አንደበት

---

# ከፍ ከፍ ያለ ምስጋና ይድረስህ

ምስጋና ይድረስህ ቸር አምላካችን
ለአበባ (2) ወራቶች ስላደረስከን

**ከፍ ከፍ በል በምስጋና**
**የምድርን በረከት ባርከሃልና**

የምድርን በረከት ባርክልን ከላይ
ባበባ (2) እንዳንቀር ፍሬዋን ሳናይ

የሰማይ ወፎችን እስቲ ተመልከቱ
ሳይዘሩ (2) ሳያጭዱ እንደሚደሰቱ

ምግብን ያገኛሉ ጎተራ የላቸው
ፈጣሪ (2) ብቻ ነው የሚመግባቸው

የኛ መጠበቡስ ለምኑ ይጠቅማል
ሃሳብን (2) ለጌታ መተው ይሻላል

---

# <u>ባለውለታዬ</u>

ባለውለታዬ ባለውለታዬ
ከአመድ ያነሳኸኝ ከትቢያ ተጥዬ } **አዝማች…**
ተመስገን ጌታዬ

በሩን ቢዘጋብኝ ስምዖን ጨክኖ
ዝቅ አድርጎ ቢያየኝ ከአይሁድ ጋር ሆኖ
እንድቀርብ ወደ እርሱ አዘዘ ጌታዬ
<u>እግሩን አጥበዋለሁ ወድቄ በእንባዬ</u> (2X)

**አዝማች…**

የቀራጭ አለቃ ቢሆንም ሥራዬ
እንድወርድ ከዛፉ አዘዘ ጌታዬ
ማዕረጌን መሸከም እስኪያቅተኝ ድረስ
<u>ቤቴ ተባረከ በኢየሱስ ክርስቶስ</u> (2X)

**አዝማች…**

ድንጋይ የጨበጡ ፈራጆች ከበውኝ
ነውሬን ዘርዝረው ጌታ ፊት አቆሙኝ
ፈረደችባቸው ኃጢአትም በእነሱ
<u>በሰላም ሂጅ ብሎ ምሮኛል ንጉሡ</u> (2X)

**አዝማች…**

የማምነውን አምላክ አውቀዋለሁ እኔ
በሰራልኝ ሥራ በዕድሜ በዘመኔ
ፍቅሩን ተሸክሚል የልቤ ትከሻ
<u>ልለየው አልችልም እስከ መጨረሻ</u> (2X)

**አዝማች…**

# ሚካኤል አማላጅ ነው

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳኢይ መልአክ ጠባቂ የእሥራኤል
የመላእክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል

አማላጅ ነው ሚካኤል (2X)
የአምላክ ባለሟል
ለነሙሴ ለሕዝበ እሥራኤል

**አዝማች…**

ፈርኦን በእሥራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ
ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ጀመር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና

**አዝማች…**

ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን
እጆቹን ዘረጋ ገሠጸው ባሕሩን
እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ
በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ

**አዝማች…**

በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላእክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን ረዳት

**አዝማች…**

መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሃለን እንድትጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ፃድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

**አዝማች…**

www.ethiopianorthodox.org

# ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያም እጮሃለሁ
ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወድሰኒ ልጄ በይኝ
} **አዝማች** (2X)

(ውዳሴ ማርያም) በሠርክ ጸሎት ላይ (ውዳሴ ማርያም) ዜማ ስናደርስ
»» ድንግል ትመጣለች »» በቤተ መቅደስ
»» የብርሃን ምንጣፍ »» ከፊትዋ ተነጥፏል
»» ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ »» ያመሰግናታል

**አዝማች...**

(ውዳሴ ማርያም) አባ ሕርያቆስም (ውዳሴ ማርያም) ምስጋና ያደርሳል
»» የቅዳሴው ዜማ »» ልብን ይመስጣል
»» በጐን ነገር ልቤ »» አወጣ እያለ
»» ዳዊት በገናውን »» እየደረደረ

**አዝማች...**

(ውዳሴ ማርያም) ለንጽሕናችን (ውዳሴ ማርያም) መሠረት ነሽና
»» አንቺን ለማመስገን »» ልቡናዬ ይብራ
»» ተፈስሒ ድንግል »» ኦ ቤተልሔም
»» ከአንቺ ተወለደ »» መድኃኔዓለም

**አዝማች...**

(ውዳሴ ማርያም) ቅዱሳኑ ሁሉ (ውዳሴ ማርያም) ዙሪያሽን ከብበዋል
»» አባ ጊዮርጊስም »» ነኢ ድንግል ይላል
»» በወርቅ ዙፋን ላይ »» ተቀምጠሽ ሳይሽ
»» ልቤ ተሰወረ »» ድንግል በግርማሽ

**አዝማች...**

(ውዳሴ ማርያም) ለንጽሕናችን (ውዳሴ ማርያም) መሠረት ነሽና
»» አንቺን ለማመስገን »» ልቡናዬ ይብራ
»» ተፈስሒ ድንግል »» ኦ ቤተልሔም
»» ከአንቺ ተወለደ »» መድኃኔዓለም

**አዝማች...** (2X)

## መስቀል ቤዛችን

መስቀል ቤዛችን ነው ድል መንሻ ኃይላችን
ከኃጢአት በሽታ የሚፈውሰን (2)
በኃጢአት ጨለማ ተውጠን ሳለን (2)
የክርስቶስ መስቀል ብርሃን ሆነልን (2)
እንድንመስለው ጌታችንን (2)
እንሸከመው ኃይለ መስቀሉን (2)
እንድንሸከም ኃይለ መስቀሉን (2)
ሰውነታችንን ማንጻት አለብን (2)

## <u>መስቀል ኃይልነ</u>

መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ
መድኃኒትነ ለዕለ አመነ (2)

# መስቀል ተመርኩዘን

**መስቀል ተመርኩዘን ወንጌል ተጫምተን
ማን ያሸንፈናል እኛ ክርስቲያኖችን
ክርስቶስ ሳለን**

ንግሥቲቷ ዕሌኒ በጣም የታደለች
በዕጣን ጢስ ተመርታ መስቀሉን አገኘች
መድኃኒት ስትፈልግ ኪራኮስን ይዛ
መስቀሉን አገኘች የዓለምን ቤዛ

ሙታን ተነስተው ያመሰገኑት
ዕጸ መስቀሉ ነው የኛ መድኃኒት
መስቀል ምርኩዛችን ጎዳናው መስቀል
ወደ ገነት እንጂ አንሄድም ሲኦል

ንዑ እናወድሳት በእለተ መስቀል
የተሸከመውን የአምላክን ቃል
ንዑ እናወድሳት ለማርያም ድንግል
አክሊለ ምዕመናን መርሀ ዘወንጌል

## መስቀል አበባ

መስቀል አበባ ነህ ውብ አበባ
ዐደይ አበባ ነህ ውብ አበባ

መስቀል አበባ .. ጥራጊ ሞልተው .. አደይ አበባ.. አይሁድ በክፋት

ጢሱ ሰገደ ... መስቀሉ ካለ በት
ተቀብሮ ሲኖር ... ሥነ ስቀለቱ

እሌኒ አገኘች ... ደገኛይቱ
አዝማች...

ግማዕደ መስቀሉ ... የጌታችን
ምስለ ፍቁር ወልዳ ... የእመቤታችን
የሚካኤል ፅላት ... ይዘው ታቦቱን
መስከረም በባተ... በአሥረኛው ቀን
ከግብፅ መጣ ... በዳዊት ዘመን
አዝማች...

የመስቀሉ ስም... ተዓምር ሠራ
ድውያን ፈወሰ ... እውር አበራ
ለምፃም አነፃ ... ጎባጣ ቀና
አጋንንት ወጡ ... ከሰው ልቦና
ፍቅር አንድነት ... ሆኖልናልና
አዝማች...

መስቀሉን ወስደው ... መስቀለኛ ስፍራ
በግሸን አኖሩት ... በአምባሰል ተራራ
የመስቀሉን ዜና ... ደስታን አበሰሩ
አሸብርቀው ደምቀው ... ለእርሱ መሰከሩ

# በመስቀል ተሰቅሎ

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለፀው
ምን ስጦታ አለን ለሱ የምንከፍለው
ምስጋና ነውና ከኛ የሚፈልገው
ቸሩ አምላካችንን ተመስገን እንበለው
} **አዝማች...**

ዓለም እስኪደነቅ ድንቅ አድርጎልናል
እንዲሁ ያለ ዋጋ ፀጋውን ሰጥቶናል
ትናንት ለእሥራኤል ሞገስ የሆናቸው
ስሙን እናመስግን ዛሬም ከእኛ ጋር ነው

**አዝማች...**

አፋችን ይሞላ በታላቅ ምስጋና
ከኃጢአቱ ባሕር ተሻግረናልና
ክቡር ምስጉን አምላክ ቅዱስ እንበለው
ኢሳይያስም በክብር በራዕይ እንዳየው

**አዝማች...**

ከቶስ ለእግዚአብሔር ምን ይከፈለዋል
ሁሉም የራሱ ነው ማን ምን ይሰጠዋል
አመስጋኝም ቢሆን ክብር ለራሱ ነው
እሱ በባሕሪው ዘላለም ምስጉን ነው

**አዝማች...**

ሙሴም ዝም አላለ ዳዊትም አልተኛ
በጎቹም ዘመሩ ለመልካሙ እረኛ
ያሬድ ተመሰጠ ወደ ሰማይ ዓለም
እኛም ከነሱ ጋር እንዘምር ዘላለም

**አዝማች...**

# አድኚኝ እናቴ

አድኚኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
ሥጋዬ ከኃጢአት ከቶ አልራቀምና
ሸክሜ የከበደኝ ብቸኛ ሆኛለሁ
<u>አትለይኝ ድንግል አደራ እልሻለሁ</u> (2X) } **አዝማች…**

የአማኑኤል እናት የተዋኅዶ አክሊል
አትጥፊ ከመሃል እንድትሆኚን ኃይል
ምንም ቢበዛብሽ የእኛ ጉስቁልና
<u>ከኛ ጋራ ከሆንሽ አለን ቅድስና</u> (2X)

**አዝማች…**

በሥጋ ደክሜ በነፍሴ እንዳልጠፋ
እማፀንሽለሁ ድንግል የእኔ ተስፋ
የመንግሥቱ ወራሽ እንድሆን አድርጊኝ
<u>መልካም ሥራን መስራት እኔን አስለምጂኝ</u> (2X)

**አዝማች…**

ተስፋዬ ነሽና እመካብሻለሁ
ግራ ቀኝ የማልል ምርኮኛ ሆኛለሁ
ስቅበዘበዝ አይቶ ተስፋ የሰጠኝ
<u>እግዚአብሔር ይመስገን ከአንቺ ያስጠጋኝ</u> (2X)

**አዝማች…**

አንቺ የሌለሽበት ጉባኤው ባዶ ነው
በቁም የደረቀ ሕይወት የተለየው
ከመሃከል ገብተሽ ሙያ የጎደለውን
<u>ሠርጉ ተደግሷል ጎብኚልኝ ጓዳውን</u> (2X)

**አዝማች…**

# <u>መስቀሉን ተሸክመን</u>

**መስቀሉን ተሸክመን በእምነት እንራመድ**
**ለሰማያዊው ክብር እንጓዝ (2) ????ከሱ ዘንድ**

እግዚአብሔር አብ ላከ አንድ.ያ ልጁን (2)
እርሱ ወደ.ልና እንዲህ አለሙን (2)

ከኃጢአት ያዳንከን ደምህን አፍስሰህ (2)
የሰላም ባለቤት አምላክ አንተ ነህ (2)

ይቅር ባይ መሀሪ ሰውን ወዳጅ አምላክ(2)
በመንፈስህ አጽናን እንዳንታወክ (2)

# ተነሱ እንዘምር

ተነሱ እንዘምር (2)
ተነሱ እንዘምር ለአምላክ በአንድ ቃል
ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል
ተነሱ እንዘምር ለአምላክ በአንድ ቃል

የአምላክ ምስጋና ምን ያሳፍረናል
እንኳንስ እሱና ሰው ይመሰገናል

ለሚያወርድልን ዝናመ ምህረት
ደግሞም ለሚሰተን እክለ በረከት

ሁሉንም በጊዜው ለሚሰጠን ጌታ
መዘመር አለብን ሁላችን በእልልታ

# እያለፈ ነው ዘመኔ

እያለፈ ነው ዘመኔ ትእዛዙን ሳልፈጽም ወየው ለኔ (2X)
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለሁ ና ብሎ ወደ እኔ (2X)

በወጣትነቴ ሳልሰራ እያየሁ አለፈኝ ብዙ አዝመራ (2X)
ከእንግዲህ በመስራት ጌታ ሆይ ልኑር ካንተ ጋራ(2X)

የማስብበት በየዕለቱ ንጹህ ልብ ስጠኝ አቤቱ (2X)
ከትእዛዝህ ውጭ በመሆን እንዳልቀር በከንቱ (2X)

እንደየስራው ለመክፈል በግርማ መንግሥቱ ሲመጣ (2X)
ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተናን የወጣ (2X)

እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ የተማራችሁ በቃሉ (2X)
ይመጣሉና በእርሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ (2X)

ትዕግሥትን በመያዝ ሁላችሁ እስከመጨረሻው ጠንክ-
ሩ (2X)
ያን ጊዜ ይሆናል በእርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ (2X)

እያለፈ ነው ዘመኔ ትእዛዙን ሳልፈጽም ወየው ለኔ (2X)
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለሁ ና ብሎ ወደ እኔ (2X)

# የዓለም መድኃኒት

የዓለም መድኃኒት ድንግል ወለተ ኢያቄም ወሃና
ላንቺ ይሁን ላንቺ ክብርና ምስጋና (2)
ተቋመ ማኅቶት ድንግል የኃጥአን ምድር አለኝታ
ችግር እንዳይገጥመን በላይኛው ቦታ
ቃል ኪዳንሽ ለኛ ይሁነን መከታ
የዓለም ፀሐይ ድንግል ክልልተ ሞገስ ወግርማ
ቦታችን እንዲሆን ከጻድቃን ከተማ
አርቂልን ከኛ ያን ከባድ ጨለማ
የማሕፀንሽ ፍሬ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር
አንቺን መርጦ ላንቺ ስለ ሰጠሽ ክብር
ቀለለልን ለኛ የችግር ቀንበር
ምልዕተ ምሕረት ወተስፋ የዓለም ቤዛ ድንግል
ጻድቃን በበረሃ በዱር በገደል
ያለቅሳሉ ካንቺ እንዲያገኙ ኃይል

# በመስቀልህ ኃይል

በመስቀልህ ኃይል በደምህ ጌታ
ሰላም ወረደ ሰይጣን ተረታ  } አዝማች…
በመስቀልህ ኃይል በደምህ ጌታ

መሬት ስትጨነቅ ከዋክብት ሲወድቁ
የአዳም ልጆች ሁሉ ይህንን ሳያውቁ
በቀራንዮ በመስቀል አንተን ሲያስጨንቁ
ስለ ፈጠርካቸው ከርህራኄ ራቁ

**አዝማች…**

አዳም በበደለ ኃጢአትን በሠራ
ሰላም ልትሰጠን ተቀበልክ መከራ

**አዝማች…**

ፀሐይ እንኳን አውቃ ጌታዋ መሆኑን
ብርሃኗን ነፍጋ አጨለመች ቀኑን
ግዙፏ ጨረቃ አውቃ ጌታዋን
ለወጠች ወደ ደም የሥራ መልኳን

**አዝማች…**

እሰይ የምሥራች ሰይጣን ተሸነፈ
ዲያብሎስ ድል ሆነ ዓላማው ከሸፈ
በትንሣኤው ብርሃን የሰው ልጅ አረፈ

**አዝማች…**

# <u>እግዚአብሔር መልካም ነው</u>

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀን መሸሸጊያ ነው } **አዝማች…**

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሦብን ሳለ በኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
<u>በመከራው ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው</u> (2X)

**አዝማች…**

አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነዓን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት
<u>እንደምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት</u> (2X)

**አዝማች…**

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
<u>ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ</u> (2X)

**አዝማች…**

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
<u>ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ</u> (2X)

**አዝማች…**

# መጽናኛዬ ነሽ ረዳቴ

በኃዘኔ በጭንቀቴ መጽናኛዬ ነሽ ረዳቴ
እመ አምላክ አደራ ድንግል እመቤቴ (2X) } **አዝማች**

ለዓለም ተዘርግቶ እጇ ባዶ ሆኗል
የራሴ ላይ አክሊል ተሸቀንጥሮ ወድቋል
ከኃጢአት ሸሽቼ መጣሁኝ ወደ አንቺ
የጐሰቆልኩትን እኔን ተመልከቺ

**አዝማች**

የእግሬ መሰናክል ለዓለም ደስታ ነው
ተስፋ ቢስ መሆኔ ለጠላቴ ድል ነው
የደስታ መፈንጫ የኤልሳቤጥ ዘመድ
እንዳልሰናከል ምሪኝ በመንገድ

**አዝማች**

ምድር ትለኛለች ተስፋ ቢስ ብቸኛ
ሳለቅስ ሳነባ አይታኛለችና
በቤተ መቅደሱ ለእኔ ዘመድ አለኝ
በኃዘኔ ሰዓት አለሁ የምትለኝ

**አዝማች**

ከአመድ የወደቀ ትንሽ ገንዘብ አለሽ
ልብሽ ራርቶልኝ ፈልጊኝ አጥብቀሽ
እምነቴ እንዳይደክም እንዳልጠፋ ልጅሽ
አድኜአለሁና በደጇ ሰላምሽ

**አዝማች**

# ስለማይነገር ስጦታው

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን } **አዝማች**

የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ሕያው እንድንሆን
ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

ንፋስን ገስጾ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እርሱ መጠጊያችን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሣኤ ሰላምን ለሰጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

ከሲዖል እሥራት ተፈተን ነፃ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...